ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ
Kinijit for Unity and Democracy Party (Kinijit)

# *በህዝብ ሀይል ጉልበትም ተንኮልም ይከሽፋሉ*

የአዲስ አበባ ህዝብን ለማስተዳደር በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወዳድረው ነበር:: ሁሉም ፕሮግራማቸውን ለህዝብ አቅርበዋል:: ኢህአዴግን ከመጥላት ብቻ ሳይሆን በማንናውም መመዘኛ ቢሆን: ከግለሰብ ነፃነት አንስቶ ዜጎች የሚፈልጉትን ሁሉ በሚፈልጉት መንገድ ለመፈፀም ቃል የገባ ፓርቲ አገኙ-ቅንጅትን:: ቅንጅት ለፌደራል ምክር ቤት ከ23-23 ለክልል ምክር ቤት ከ138-137 ወንበር አሸነፈ::

በማያሻማ ሁኔታ የአዲስ አበባ ህዝብ ቅንጅት እንዲያስተዳድረኝ ፈቅጃለሁ አለ:: ይህን ፍላጎቱን ማንም በምንም መልኩ: በምንም ስልጣኑ: በምንም ተንኮሉ ሊቀይረውና ሊለውጠው አይችልም::

በወቅቱ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ቀውስ: የአዲስ አበባ መስተዳድር ጉዳይ ከፍተኛ ትርጉም አለው:: ለኢህአዴግ: ሰላምና መረጋጋት ለማስፈን መቻሉን ለአለም አቀፍ ሕብረተሰብ ማስረጃ ለማድረግ ይጠቅመዋል:: በአዲስ አበባ ህዝብ ላይ እየወሰደ ላለው የበቀል እርምጃ የማስፈፀምያ መሳርያ ለማግኘት፤ በዚህም ቅንጅት ላይ ጥላቻን ለማስፋፋት ይፈልገዋል::

ተመራጮቹ ምክር ቤቱን ተረክበው በአዲስ አበባ ህዝብ ላይ አፈናውን ለማጠናከር መሳርያ ከሆኑለት: የህዝብ ቁጣ ሲብስ ካበረዱለትና ካፈኑለት: ዕድሜ ይሰጣቸዋል:: የመረጣቸውን ህዝብ ፍላጎት ማሟላት ከሞከሩ: የህዝብን መብት ጠብቀው የመሪዎቻችንን መፈታት የሰላማዊ ተቃውሞ ጥሪ: ህጋዊ ሰላማዊ ሰልፍ: ሥራ ማቆም ጥያቄ ማስተናገድ ከጀመሩ: በተደገሰላቸው መሰረት: በሙስና: ባስተዳደር ብልግና በስንፍና: ባስተዳደር በደል በመወንጀል ለማሰር: ለማባረር: ለማውረድ: ቅንጅትን ለማሳጣት ዝግጁ ሆኖአል::

የአዲስ አበባን መስተዳድር ስለመረከብ ጉዳይ: በተደጋጋሚ ለስድስት ጊዜ እየተደረገ ያለው ሙከራ የህዝብን ድምፅ ለማክበር: የአዲስ አበባ ህዝብ በመረጠው ፓርቲ እንዲተዳደር ኢህአዴግ ፈልጎ ነው ብሎ ማሰብ እራስን ማታለልና የዋህነት ነው:: ኢህአዴግ በፀጥታ ሀይሎች አማካኝነት ወዳጆቻችን በሚላቸው አምባሳደሮች የዲፕሎማሲ ስነምግባር የጎደለው ተባባሪነት: ከአድርባይነትም ይሁን: ከስልጣን ጉጉት: ከሞራል ዝቅጠት የመነጨ ክህደት በተለወሱ ግለሰብ ተመራጮች በአፈና በማስፈራራት በማሳደድ መግቢያ ቀዳዳ በጠፋቸውና በተጨነቁ ግለሰቦች በመጠቀም የተንኮል ሴራውን ሲሸርብ ሰንብቷል::

በዚህ በያዝነው ሳምንት ብቻ በርካታ ተመራጮች ከቤታቸው ከመስሪያቤታቸውና ከመንገድ እየታፈሱና እየተለቀሙ ማስጠንቀቅያና ማስፈራራት ደርሶባቸዋል:: አብዛኛ ዎቹም የህዝብ ፍቅርና ወገናዊነት: የቅንጅት መሪዎች መስዋዕትነትና አደራ: ዘላቂ የሆነ የመንፈስና የአካል ነፃነት እየታያቸው ለማስፈራራትና ለማባበል እንደማይንበረከኩ በቆራጥነትና በጀግንነት በመግለጽ ላይ ናቸው::

ብዙ ተመራጮች ባሳለፍነው ጥቂት ቀናት በሀሰት መረጃ መሳሳታቸውን በማመን: የቅንጅትን መንፈስ መልሰው ለብሰዋል:: በቃልና በፅሁፍ ፊርማቸው እንዲነሳ ጠይቀዋል::

የምርጫ ቦርድና የፀጥታ ሀይሎች ማስፈራራት የህሊና ነፃነት ስለነሳቸው፡ በአካል ለመቅረብ በመፍራት ብዙዎቹ ተቃውሞዋቸውንና ስማቸው እንዲሰረዝ ማመልከቻቸውን በፋክስ በመላክ ላይ ናቸው። የበለጠ የሚያሳዝነውና የሴራውን ጠንሳሾች ሊያሳፍር የሚገባው ግለሰቦቹ ሳይፈቅዱና ሳያውቁ በስማቸው ፊርማ ተፈርሞ መገኘቱ ነው። ለምሳሌ ም ያህል ከነዚህ ግለሰቦች መሀከል አንዱ የሆኑት በስብሰባ መሀል ይህንኑ ማጋለጣቸው ሲታወቅ በፍራቻ ራሳቸውን ደብቀው የተቀመጡ መኖራቸውም ይታወቃል።

የቅንጅት መሪዎችን የፖለቲካ እስረኝነት ጥያቄ ለማደብዘዝ የተቀነባበረው ሴራ አካል የሆነው ይህ እንቅስቃሴ በጠቅላላ የአዲስ አበባን ህዝብ ከመናቅ ፡ ከእብሪትና ከፀረ ህዝብነት የመነጨ ነው። በዚህ ሴራ የተሳተፉ የፖለቲካ ህይወታቸውን የቀጩ በህዝብ የተተፉ የህሊና ቁስል የማይሽር ጠባሳ የሚያሳድርባቸው መሆኑን ካሁኑ ሊገነዘቡ ይገባል።

ትርፉ ትዝብት ሆኖ ይቀራል እንጂ የህዝብ ቁጣና ብሶት እያየለ መጥቷል። ቅንጅት ለአንድነትና ዲሞክራሲ ይህን የህዝብ ቁጣ ኃላፊነት በተሞላው መልኩ ወደ ህዝባዊ ሀይል በመቀየር እብሪተኞችን ትምህርት እንዲያገኙ ለማድረግ ከህዝብ ጎን ቆሟል። በዚህ መሰረት ቅንጅት በድጋሚ የሚከተለውን ጥሪ ያስተላልፋል፤-

1. ቅንጅትን ወክላችሁ ለአዲስ አበባ መስተዳደር ተመርጣችሁ ለመረከብ ተገዳችሁም ሆነ የተሳሳተ መረጃ ተከትላችሁ ፊርማ ያሳረፋችሁ ለምርጫ ቦርድ በጽሁፍ የዚህ ሴራ ተካፋይ ለመሆን ያለመፈለጋችሁን በቆራጥነት አቅርቡ። ታሪክ ስሩ።

2. ይህንን በማስተባበር ላይ ያላችሁ ወገኖች፤ ጉዳያችሁ ከይቅርታ በላይ ከመሆኑ በፊት እንቅስቃሴያችሁን በአስቸክዋይ አቁሙ።

3. እስከአሁን የዚህ ሴራ ሰለባ ያልሁናችሁ የቅንጅት ተመራጮች፤ የወሰናችሁት ውሳኔ የህዝብ ወገን መሆናችሁን ስለሚመሰክር፤ ህዝብና ፓርቲያችን ይኮራባቹሀል፡ እናንተም ልትኮሩ ይገባል።

4. የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ የሆናችሁ፡ የወገንን የሀገር አደራ ለስልጣን ጥማተኞች አሳልፎ ከመስጠት በመቆጠብ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን ተሰለፉ።

5. የኢትዮጵያ ህዝብ በጠቅላላ በቅንጅት አማካኝነት የሚቀርብለትን የትግል መርሀ ግብር ለመተግበር ራሱን አዘጋጅቶ በትእግስት እንዲጠብቅ ቅንጅት ጥሪውን ያስተላልፋል።

**ድል የህዝብ ነው**
**ቅንጅት ለአንድነትና ዲሞክራሲ ፓርቲ**
**አዲስ አበባ**

***ሚያዝያ 14 1998 ዓ.ም.***